
# <u>እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2017 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

በኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሁም ከመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀን ወደ ቀን የመዳከም ሁኔታ የተስተዋለባቸው ቢሆንም፤ ከአስሩ ቀናት አጋማሽ በኋላ ከተፈጠረው የደመና ሽፋን በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ለጥቂት ቀናት አነስተኛ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የምዕራብ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ተስተውሎባቸዋል። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከተፈጠሩ ጠንካራና ዝናብ ሰጪ ደመናዎች በአንዳንድ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ. በላይ ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል በአቦቦ 49.2፣ በላይበር 38.9፣ በአርጆ 36.4፣ በዲላ 34.7፣ በአይከል 30.1፣ እንዲሁም በቦሬ 30.0 በሚ.ሜ. ተመዝግቧል።


ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-116 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከትግራይ የምዕራብ፣ የደቡብና የመካከለኛው ትግራይ፤ ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር፣ የምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ ዞን እንዲሁም ደቡብ ወሎ፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ አብዛኛው ኦሮሚያ፤ ሀረሪ እንዲሁም ከአፋር ዞን 3 ና 5፤ ከሶማሌ የቀብሪደሀር፣ የደገሀቡር፣ የፊቅ፣ የአፍዴርና የጅግጅጋ ዞኖች ከ2-10 ቀናት ያህል ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2)።

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛ ጋር ሲነጻጸር ከትግራይ የመካከለኛው ትግራይ፤ ከአማራ የሰሜን ጎንደር ሰሜናዊ ክፍል፣ ከአፋር የዞን 1፣4ና 5፣ ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የአሶሳ፣ የመተከልና የከማሺ ምዕራባዊው ክፍል፤ ጋምቤላ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከከፋ ዞኖች በስተቀር፤ ከኦሮሚያ የምዕራብ ሐረርጌ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች፣ ኢሉአባቦራና ጅማ፤ እንዲሁም ከሶማሌ የቆራሄና የዋርዴር ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3)።


ካርታ1   ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ3 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




# <u>እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

# <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

በኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የሰሜንና የሰሜን ምሥራቅ እንዲሁም የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ከነበራቸው የደመና ሽፋን በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ለጥቂት ቀናት አነስተኛ ዝናብ ያገኙ ቢሆንም፤ ብዙውን ጊዜ ደረቅ የአየር ሁኔታ ተዘውትሮባቸዋል። ይህም በመሆኑም በተለይም በመደበኛ ሁኔታ ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍል ዝናብ መውጫው ስለሆነና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሄዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም፤ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ለጥቂት ቀናት የተገኘው አነስተኛ እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል። በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት በአካባቢው ተገልብጦ በድጋሚ ለተዘሩ ሰብሎች አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር እሙን ቢሆንም፤ በአንዳንድ አካባቢዎች ሰብሎች እየደረሱ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የሰብል ስብሰባ እየተከናወነ ባለባቸው ቦታዎች የነበረው እርጥበት አሉታዊ ጎን እንደሚኖረው ነው። በሌላ በኩል በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው እርጥበት በተለያ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር እሙን ነው። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚካሄድባቸው አካባቢዎች ላይ ዘር ለመዝራትና እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደርች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደነበረው ይገመታል (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን ገፅታ በተመለከተ በአንዳንድ የተፋሰስ ኪስ በታዎች ላይ የተሻለ የእርጥበት መጠን የተስተዋለባቸው የታችኛው ተከዜ፣ የታችኛውና የመካከለኛው አባይ፣ አብዛኛው የባሮአኮቦ፣ የኦሞጊቤ፣ የታችኛውና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ጥቂት የታችኛው አዋሽ እንዲሁም ጥቂት ኪስ በሆኑ የላይኛው ዋቢሸበሌና አብዛኛው የገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ሲሆኑ፤ አብዛኛው የአዋሽ፣ ጥቂት የላኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የታችኛው ዋቢሸበሌ እንዲሁም ጥቂት ኪስ በሆኑ የአባይና የተከዜ ተፋሰሶች ላይ እና በሌሎች የተፋሰስ ክፍሎች ላይ ግን ከፊል ደረቅና ደረቃማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10/2017 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2017 የሚኖረው
## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዚህም ሌላ ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተነሳ በተለይም በአንዳንድ የምዕራብና የደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ወለጋ፣ አርሲና ባሌ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች፤ ጋምቤላ፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ የምዕራብ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ምዕራብ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የወላይታ እና የደቡብ ኦሞ፣ የጉራጌ፣ የሲዳማ፣ የጌዲዮ እና የሰገን ህዝቦች እንዲሁም ከሶማሌ ክልል ደጋህቡር፣ ፊቅ፣ ቀብሪደሃር፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ጎዴ በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ደመናዎች በሰሜንና በደቡብ ወሎ እንዲሁም በአዲስ አባባ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ ዝናብ ይኖራል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡

## እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

ከላይ በትንበያው ላይ እንደተገለፀው በሚቀጥለው የኦክቶበር የሁለተኛዉ አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በአብዛኛው ለግብርናው ዘርፍ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የእርጥበት ፍላጎት ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ በመጠኑም ቢሆን የሚገኘዉ እርጥበት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ይገመታል።

በተጨማሪም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ የእርጥበት እጥረት በሚያጋጥማቸዉ ዘግይተዉ በተዘሩ የመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለዋግ መፈጠር ምቹ ሁኔታዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ አርሶ አደሮች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ሰብሎች እየደረሱ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የሰብል ስብሰባ እየተከናወነ ሲሆን፤ እርጥበት የሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች እርጥበቱ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## <u>እ. ኤ. አ ከኦክቶበር 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በበዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ትንበያው የሚያመለክት በመሆኑ፤ ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይም የተሻለ የእርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል።

በዚሁ መሰረት የላይኛው ተከዜ፣ አብዛኛው መረብ ጋሻ፣ የላይኛው አባይ እና ኦሞ ጊብ የተፋሰስ ቦታዎች ላይ ከፊል ደረቅና ደረቃማ የአየር ሁኔታ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንፃሩ በተቀሩት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም መደበኛ የሆነ የዝናብ ስርጭት በሚጠበቅባቸው ቦታዎች ላይ መጠነኛ ዝናብ ስለሚኖርና የወንዞች ሙላት ሊከሰት ስለሚችል ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል$